# አሉላ አባ ነጋ

## ታሪካዊ ልቦለድ

በማሞ ውድነህ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
፲፱፻፸፱

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
Kuraz Publishing Agency

ስልክ ቁጥር
Tel. } 112719

ፖስታ ሣ. ቁ.
P. O. Box } [illegible]

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ADDIS ABABA
ETHIOPIA

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ።
All Rights Reserved

[illegible]

[illegible]

# ለዶጋሊ ድል

## መቶኛ ዓመት መታሰቢያ

## የተዘጋጀ

# ምስጋና

ለዚህ መጽሐፍ ጥናትና ዝግጅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ 'የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት' ፣ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲዉ የታሪክ መምህር የሆኑት ዶክተር መርዕድ ወልደ አረጋይ ላደረጉልኝ ትብብር ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።



## እንዲህ አለ አሉላ ።

ተሻገረ ቢሉት ቀይ ባሕርን ጠላት ፣
አሉላ ተቆጣ ነደደ እንደሳት ።
'ማን' አለ 'ፈረሴን ወልውል ጉራዴዬን ፣
አውርድ ከግድግዳ ጦርና ጋሻዬን ፣
ማንም አይረግጣትም ውዲቱን አገሬን ።
ምታ ፣ ነጋሪቱን ንፋ መለኸቱን ።
ጀግናው ሁሉ ይከተት ይሰለፍ ይታጠቅ ፤
አገር መደፈሩዋን ይነገረው ይወቅ ።'
ሰማ ሠራዊቱ የጠላትን ድፍረት ፤
ጥቃቱ ሆነበት የመረረ እሬት ።
'እንሒድ እንዝመት ጠላትን እንውቃ ፤
ክንዳችንን ይየው ትዕግሥታችን ይብቃ !'
በረብረቡ ገደል በጊንዳ ቁልቁለት ፤
የዳማስን ሜዳ የሰሐጢን ኸረት ፤
የአሉላ ሠራዊት ተርመሰመሰበት ።
አገኘው ጠላቱን ተድአሊ ላይ ሠፍሮ ፤
ምሽጉን ገንብቶ መድፉን አነጣጥሮ ።
'በለው !' አለ አሉላ 'ግባ ተደባለቅ ፤
አባየው ክንድህን ማንነትክን ይወቅ ።'
አልተረም አንጀቱ ጢሶ እንደ ነደደ ፤
የጠላቱን አንገት እያወራረደ ፤
ጣለው በጉራዴ አጨደው ከመረው ፤
ተድዓሊ ዕልል አለች ፣ አሉላን ደስ አለው ።
ከዚያ በኋላ ነው ፤
አሉላ እንዲህ ያለው ፣

# ወይ ያች ዕለት

በመጀመሪያ የተኮሳት ጥይት ዒላማውን ሳተች ። ሁለተኛዋ ዱሉ የቀኝ ቀንድ መታች ፤ ሦስተኛዋ ባከነች ፤ አራተኛዋም ተሠለበች ፤ አምስተኛዋ የግራ ቀንድ መታች ። የተሰጡት ጥይቶች አለቁ ። ወጣቱ በንዴት እየጨሰ ሰናድሩን ከድግኑ ተና አደረገው፣ በትልቅ ዶጉሬ ሥር ተተክሎ የነበረውን የከብት ግንባር እየንት በጥላቻ ተመለከተው ። ሦስቱንም ጥይቶች አባክኖ እናቱን በኩርኩም ሊያስፈልሰው የተሰለፈ ጠላት ሆኖ ታየው ።

«አንደኛትክ ፤ በምን የተነሣ ሦስት ጥይት ታባክናለህ» ብለው ባሻይ ፈንጃ ሰናድሩን ከጁ ነጠቁና ክንዱን ጥርቅም አድርገው ይዘው ፤ ይተናነቃቸው የነበረውን ቁጣ ከላይ ላይ እያፈሰሱበት ፤

«ስትተኩስ ሆድህን ሸላገህ ምራቅህንና ትንፋሽህን ውጠህ ሰውነትህን አስቆጥተህ መንፈስህን ሰብስበህ ነው ፤ ቃታ መሳብ አልነበረምን» ብለው ክንዱን ለቀቅ አደረጉና እንደገና ጆሮውን ይዘው ወደ ግፍትልትል እያደረጉ ፤

«ከዒላማህ ላይ ስታነጣጥር ትንፋሽህን ከለቀቅክ ፤ ሰውነትህን ካላላክ ቅብጥታለህ ብዬህ አልነበረምን ይህን ነገር አባቴ ቢሰማ ጭንቅላትህን በኩርኩም ነው የሚያፈልሰው ። ሁለተኛ እንኳን ከኔ ፊት ቀርቶ ፤ 'ተኩስ ሳተ' የሚል ወሬ እንዳልሰማ» ብለው አንድ ጊዜ ከአናቱ ላይ ለቆቅ አድርገው ለቀቁት ።

ባሻይ ፈንጃ ፤ በጠዋት ተነሥተው ከቤታቸው እልፍ ብሎ በነበረው ሸንኮ ተቀምጠው ፤ ሰናድራቸውን ከደንጋይ ላይ አጋድመው የጠዋቱን ፀሐይ ሙቀት በሰውነታቸው ውስጥ ሲያከማቹ በነበሩበት ሰዓት ፤ ወጣቱ አሰሳ የዝቋላ ሚካኤል መም

የአሉላ ጀግንነት በዘላቂ ደረጃ ታውቆ ለመታሰቢያነቱ መሠረት ሲጣል፣ በሥነ ሥርዓቱና በቦታው ለመገኘት በመቻሌ ዕድሌ በፊትም ሆነ በኋላ የራስ አሉላን ታሪክና ለአገሩ ሕዝብ ለማቅረብ ላደረግሁት ሙከራ ማበረታቻ ሆኖኛል።